<u>ሰነድ</u>

*የመጀመሪያ ዕትም*

# <u>ጋህነን/ግ በጋምቤላ ሕዝብ ችግር ላይ ያለው አቋም</u>

በኢሕዲግ ቀያሽነት የሚደረገው ሕዝብን የማፈን ተግባር ቡድናዊን ስልጣን ተገን በማድረግ በልግዛ አልገዛም ትንቅንቅ በሀገሪቱ ያሉትን የክልል ሕዝብ ፖለቲካዊ፤ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ሊፈቱ አይችሉም።

ዓላማችን በአሁኑ ወቅት የደረሰበት የዕድገት ደረጃ የሕዝብ ንቃተ ህሊና ከምንም ካለመቁጠር ኢሕዴግ የታሪክ ተወቃሹ የመሆኑ ያህል ክስተቶች ሲለወጡ አብሮ የማይለወጥ የፖለቲካ ድርጅት ሕዝብን የማፈንና የማጭበርበር ተግባሩን እየቀጠለበት ይገኛል።

በአሁኑ ወቅት ያለውን የዓለም የፖለቲካ ዕድምታ ለሕዝብ ለህብረተሰብ ወይም ለግለሰብ እንዲያመች ተደርጎ በተቀየሰበት ወቅት የሕዝብ ሰበሐዊ መብቶች ሐሳብን በነፃ የመግለፅ ፤ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ፤የመሰብሰብ፤በገሀድ ለሕዝብ በተሰጠበት ዓለም ሕዝብ ሀሳቡን በሚገልፅበት ዘመን በሀገራችን ኢትዮጵያ የኢሕዴግ መንግስት እነዚህ ዲሞክራሳዊ መብቶች በመገደብና በመከልከል ሕዝብን በአፈና ሲያዋክብ ይገኛል።

የአንድ ቡድን የስልጣን መጨበጥ ወይም ስልቱን እየለዋወጠ ለብዙ ዓመታት ካለ ሕዝብ ፍላጎት በስልጣን ላይ የሙጥኝ ማለት ጊዜ የለፈበትና የወቀቱ አሳፋሪ ተግባር ከመሆኑም አልፎ የአለፉትን መንግስታት አወዳደቅ ወርደት ካለመረዳት ወይንም ሕዝብን ከመናቅ የተነሳ ለሆን ይችላል። ለምስክርነት ያህል ከፒተር ኤግ መፃሕፍ(underatanding global security) ውስጥ በተለያዩ ወቅቶች በገገር መደቦች የተፈፀሙ አስር የዓለማችን ዘር ማጥፋት ወንጀል መነሻቸው ሕዝብን ማፈንና መብቶቻቸውን በመገደብ የአንድ ብሔረሰብ የበላይነት በማንጸባረቅ የስልጣን ጥማቸውን ለማርካት ሲሉ የዘር ማጥፋት ወንጀሎችን እንቅስቃሴ ያሳየናል።

| ተ.ቁ | ፖሊስ አውጪ | ዓ.ም | የተጎዳው ሕዝብ ስም | የተፈጀው ሕዝብ ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| **1** | **ሞንጎሊያን** | **1215-1279** | **ቻይናዊያን** | **18.8 ሚሊዮን** |
| **2** | **ሞንጎሊያን** | **1220-1222** | **ፐርሻውያን** | **6 ሚሊዮን** |
| **3** | **ቱርካዊያን** | **1915-1917** | **ሮማኒያውያን** | **1.3 ሚሊዮን** |
| **4** | **ፓክስታናውያን** | **1917-1918** | **ቫንጎላዊን** | **1.5 ሚሊዮን** |
| **5** | **ናዚ ጀርመን** | **1933-1945** | **ጁሽ** | **6 ሚሊዮን** |
| **6** | **ናዚ ጀርመን** | **1940-1945** | **ኤሻውያን** | **10.5 ሚሊዮን** |
| **7** | **ፖላንድ** | **1945-1948** | **ጀርመናውያን** | **1.6 ሚሊዮን** |
| **8** | **ቻይናወያን** | **1959-2003** | **ታይዋን** | **1.6 ሚሊዮን** |
| **9** | **ናጄሪያውያን** | **1966-1970** | **ኤቮሳዊን** | **1ሚሊዮን** |
| **10** | **ሱዳን** | **1983-2003** | **ደቡብ ሱዳናውያን** | **1.5ሚሊዮን** |

እነዚህን ክስተቶች ስንመለከታቸውና በደንብ ሰናጤናቸው በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ኢትዮጵያ እየተደርጉ ካሉት ሕዝብ ከሕዝብ ፤ብሔር ከብሔር እና ጎሳ ከጎሳ ላይ እንዲነሳ የገዛ ዜጋውን ፤ውንድሙን እንዲጠላ ፤ንብረቱን እንዲያወድም አልፎተርፎም እንዲገለዉ በሚደረገው ሥርዓት አልበኝነት የተሞላበት የፖለቲካ እንቅስቃሴ

የሚያንፀባርቀው ያለው ገዢ መደብ ጥቅማቸውን ለማስከበርና በሥልጣን ላይ የመቆየት ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ እነዚህ ሕዝቡን የመለያየትና የመከፋፈል አጀንዳቸውን ይጠቀማሉ ። ለዚህ ነው ያየናቸው የዘር ማጥፋት ወንጀሎች በተለያዩ ወቅቶች ሊፈፀሙ የቻሉት።

በዚህም መራራ ትግልና አሰልቺ ጉዞ ውስጥ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ሕዝባቸው የተነፈጉትን ነፃነት ለማስመለስ ሲሉ አያሌ የአፍሪካ መሪዎች ተወድቀዋል። ለምሳል ያህል አንጋፋው የደቡብ አፍሪካ ብሔራዊ ኮንግረስ(Africa National congress) ለሕዝባቸው ሲሉ እራሳቸውን አሳልፈው በመስጠት ከገዢው መደብ ጋር ያደረጉት ከፍተኛ ትግል ውጤቱ አሁን ላለው የደቡብ አፍሪካ ሕዝብ ነፃነት መጎናፀፍ መነሻ ነው።

# የጋምቤላ ሕዝብ ችግሮችና መንስዎቻቸው

አንድ የሕክምና ባለሞያ ለበሽተኛው መድኃኒት ከማዘዙ ፊት መጀመሪያ ማድረግ የሚገባው የበሽተኛው ሁኔታ ፤ መነሻ ምልክቶቹን ከጠየቅና ከተረዳ በኃላ ውሳኔ ላይ ከመድረሱ በፊት ለችግሩ ዘላቂ መፍቴ ለማግኝት ሲል በቤተ-ሙከራ ምርመራ ማካሄዱ የግድ ነው።

ይህን መነሻ በማድረግ የጋምቤላ ሕዝብ በተለያዩ የአገዛዝ ዘመናት የደረገበት የስልጣን መለዋወጥና መቀያየር ለሕዝቡ  የፈየዱት አንዳችም ቁም ነገር የለም። ምክንያቶቹም:-

**1.**ንቃተ ሕሊና (conscience)

**2.**አገልግሎት (service provision)

**3.**ፖሊሲ (policy)

**4.**ሥልጠን (power)

እነዚህ ከላይ የተቀስናቸው የሕዝብ ንቃተ ሕሊና እድገት አለመኖር ፤ ግልፅ ፖሊሲ አለመኖር፤አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አለመቋቋምና የተፈራረቁት ገዢ መደቦች በስልጣን ዘመናቸው ሕዝብን በትክክል አለማገልገል በሕዝባችን ላይ የጣለው ጠባሳ በጥልቀት እንድንመለከታቸው የደርገናል።

# የአፄ ምኒሊክ የአዛዝ ዘመን

የጋመቤላ ሕዝብ ባህሉና ሐይማኖቱን ለዘመናት ጠብቆ የኖረ ሕዝብ ከመሆኑ አልፎ የራሳቸው የሥልጣን ሐረግ የነበራቸውቸውና እራሳቸውን በራሳቸው ሲተዳደሩና ሲመሩ የኖረ ሕዝብ ነው።የነበራቸውም ንቃተ ህሊና ሕዝቡን ከማስተዳደር ሊያግዳቸው አልቻለም።

በዘመኑ የነበረው የግዛት መሳፍንት እና የመሬት ባለቤትነት ምኞት የተጠናወታቸው ገዢ መደቦች የጋምቤላን መሬት ተቀሜታና ድንግልነቷን በመረዳት አፄ ምኒሊክ የጋምቤላን ሕዝብ ለመግዛት ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበራቸውም።

በዚህም የተነሳ ለብዙ ዘመናት በጠንካራ ሠራተኛነቱ የሚታወቀው ሕዝብ እንደበፊቱ በራሳቸው ጉዳይ የመወሰን መብታቸው በጥቅም ተፋለሚ ሀይሎች ተነጥቆባቸው የሩቅ ተመልካች እስከ መሆን ድረስ ደርሳዋል። ለዚህ ሁሉ መነሻ ምክንያት የአፄ ምኒሊክ ምኞትና ሌሎች ሀገሮች ሲካሄድ የነበረው የግዛት ወሠን ማስፋፋት ያለውን ገዥ መደብ የገቢ ምንጭ ማሳደጊያ ሕዝቡን ለባሪያ ገዥነት በመዳረግ ያደረጉት የጭቆና ተግባራት

ለሕዝቡ ዕድገትና ጥቅም እንዳልሆነ በግልፅ እንረዳለን። በዚህም ሳያበቃ ከአፄ ምኒሊክ ውድቀት በኃላ የመጣውም ገዥ መደብ የተለየ ተግባር ሲፈፅም አልታየም።

## የአፄ ኃይለስላሴ የአገዛዝ ዘመን

የታሪክ ምሁር የሆኑት ዶ.ር ሮበርት ኦ. ኮሊን እንደሚሉት ከሆነ በመፃፈቸው (shadow on the grass) ወላጅ አልባ የሆነው የሶሪያ ሀገር ተወላጅ የሆነውን ማጂድ አቡድ እ.አ.አ. 1884 ዓ.ም በጆርዳን ወንዝ አጠገብ በሚገኝ አነስተኛ መንደር ተወልደው በኢየሩሳሌም የሕፃናት ማሳደጊያ ውስጥ ያደጉ ሲሆን ለአፄ ኃለስላሴ ፖሊሲዎች ተግባራዊነት ከፍተኛ ሚና ከተጫወቱት የውጭ ሀገር ተወላጆች መካከል አንዱ ነው ። ማጂድ በ19 ዓመቱ የዴንማርክ ሚሽነሪ ተከትሎ ኢትዮጵያ ከገቡ በኃላ በነበራቸው የመንፈሳዊ ጥንካሬ ከልጅ እያሰና ከራስ ተሰማ ጋር መልካም ግንኙነት ለመፍጠር ጊዜ አልወሰደባቸውም ።

ማጂድ በነበራቸው የተለያዩ ቋንቋዎች ችሎታ የተነሳ የአማርኛን ቋንቋ ችሎታቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት በወቅቱ ለነበረው ገዥ መደብ ዓላማ ለማሳካት ማጂድን መጠቀሚያ አድርገውታል ። በዚህም የተነሳ ገዥ መደቦች በጋምቤላ ለነበራቸው የኢኮኖሚ ምኞት ለማሳደግ ሲሉ እ.አ.አ. 1914 ዓ.ም ምዕራብ ኢትዮጵያ ጎሬ አጠገብ ጉሞሮ በሚባል ቦታ ላይ መሬት ተሰጣቸው። ይህን ሁለታ ለመመለስና ተወዳጅነት ለማትረፍ ሲሉ በደመ-ነፍስ ይንቀሳቀስ የነበረው ማጂድ እ.አ.አ 1916 ዓ.ም የጋምቤላ ሕዝብ ለኢትዮጵያ እውቅና አልሰጡም በሚልና በግዴታ ኢትዮጵያዊ መሆን አለባቸው በማለት ያነሱት ሐሳብ በጋምቤላ ሕዝብ ተቀባይነት በማጣቱ ከአራት መቶ ታጣቂዎች በላይ አስከትሎ በባሮ(ኡፔኖ) ወንዝ ዳርቻና ኢታንግ ላይ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሰላማዊ ሕዝብ ፈጅተዋል።

በዚህም የተነሳ በጋምቤላ ሕዝብ ላይ ያደረጉት ሙከራ ምንም እንኳን ተቃውሞ ቢገጥመውም ለኢትዮጵያ ሹማሙንቶች እንደ ድል ተቆጥሮላቸዋል በ1932 ዓ.ም በጃንዊ (ኃይለስላሴ) የኢትዮጵያ ድንበር ወስን ተጠሪ ሆነው ተሾሙ ። አቶ መጂድም ድጋሚ በተሰጣቸው ሥልጣን በመጠቀም ሹማምንቶችን ለማስደሰት ሲሉ እንደገና 360 ታጣቂዎችን አስከትለው ከጊሎ ወንዝ እሰከ አኮቦ ዳርቻ ባለው ሠላማዊ ሕዝብ ላይ ይህ ነው የማይባል አሰቃቂና ዘግናኝ የግድያ ወንጀሎችን በሕዘብ ላይ ፈጽመዋል።

## የደርግ የአገዛዝ ዘመን

የደርግ መንግስትም ከላይ ከአየናቸው ገዥ መደቦች የተለየ አላማና የአገዛዝ ስልት ይዞ አለመምጣቱ ለመረዳት አያዳግትም። የደርግ መንግስት በጋምቤላ ሕዝብ ላይ የተሞከረው ዘርን የማጥፋት ሥልት አሳዛኝና አሳፋሪ ከመሆኑ የተነሳ ለዘመናት ለረሳ የማይችል እሰከፊ ተግባር ነው።

ይህም የአለፉትን ገዥ መደቦች የግዛት መስፋፋት ዕቅድ መልኩን ቀይሮ በመምጣት የደገኛውን ሕዝብ በሰፈራ መልክ ለማምጣት ራሀብን ተገን በማድረግ የተፈጸሙት ተግባር የጋምቤላን ሕዝብ ፍላጎትና እምነት ከግንዛቤ ሳያዝገባ የተደረገ ከመሆኑ አልፎ የሰፈራ ፕሮግራሙ ለአካባቢው ደን መጨፍጨፍ ፤ነባሩን ሕዝብ ከለመደው የመኖሪያ አካባቢው ማፈናቀልና ለሕብረተሰቡ አለመረጋጋት ከፈተኛ አስተዋፆ አበርክተዋል።

ከዚህም አልፎ ተረፎ የደርግ መንግስት የሕዝብ የትምህርት ደረጃ ከማሳደግ ይልቅ ሕዝቡን ለወታደራዊ ተግባራት ብቻ ሲጠቀምባቸው አልፏል:: ለሕዝቡም ያደርግ የነበረው ብሔራዊ ውትድርና ፤መለዮ ለባሽ ፤ወዶ ዘማች፤ጦር ሠራዊት፤ሚሊሻ፤ቁምጣ ለባሽ ወዘተእተባለ ስማቸውን እየቀየረ አምራች የነበረውን የህብረተሰብ ክፍል ለግል ጥቅም ማሳኪያ ሲል በየጦር ግንባሩ ሲማግዳቸው ቆይቷል/አልፈዋል::

## የኢሕዴግ የአገዛዝ ዘመን ከ1991 እስከ አሁን

*የጋምቤላ ሕዝብ ተጎጂነቱ ከመጀመሪያው ገዥ መደብ አንስቶ አሁን የኢህዴግ መንግስት  እየገዛ እስከ አለበት ቀን ድረስ ጭቆናውና በደሉ አላበቃም::*

*ለጋምቤላ ሕዝብ የአለፉት  መንግስታትና አሁን ያለውም መንግስት ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ ከመሆኑ በቀር ምንም የፈየደው አንዳችም ነገር የለም::*

*ያአለፉት መንግስታት በጋምቤላ ሕዝብ ላይ የፈፀሙት ግፍና በደል ሕዝቡ አሜን* ብሎ አልተቀበለውም  የራሱ ነፃነትና ዲሞክራሳዊ መብቱን ለማስጠበቅ ሲል የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ሲደረጉ ቆይተዋል:: ለዚህም ነው የደርግን መንግስት ለመጣል እ.አ.አ በ1977 ዓ.ም በጋህነን/ግ ድርጅት ጥላ ሥር በመሰባሰብና በመደራጀት ከሌሎች ጭቁን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፈጠሩት ድርጅቶች ጋር በመጣመር አብሮ ደርግን ለመጣል የተንቀሳቀሱት:: በዚህም እንቅስቃሴ የጋምቤላ ሕዝብ እስከ ደርግ መውደቅ ድረስ የበኩሉን አበርክቷል::

እ.አ.አ 1991 የተገኘው ለውጥ ለጋምቤላና ሌሎች ጭቁን የኢትዮጵያ ሕዝብ ድርጅቶች ጋር በፈጠሩት ቅንጅት የተገኘ ነው:: ለዚህም ነው የለውጡ ተጠቃሚ ለመሆን በከፍተኛ ደስታና ጉጉት መንግስቱን የተቀበሉት:::

አቀባበላቸውም ከዚህ በፊት የነበሩት ገዥ መደቦች ይከተሉት የነበረውን ሥውርና አድሎዊ አሠራሮች ያበቃሉ በሚል ተስፋ ከሽግግር መንግስት ጀምሮ መንግስት እስከ ተቋቋመበት ጊዜ ድረስ በመለው ሀገሪቱ በሚደረጉ የድህነት ጥበቃ፤የሠላም መረጋጋትና በድንበር በመከለከል ተግባር ላይ ያለማንገራገር በሙሉ ልቡ ተሳትፋል::

*ይሁን እንጂ የኢህዴግ  መንግስት ለጋምቤላ ሕዝብ የጭቃ ውስጥ እሾክ ሆኖበት ከመንግስት ይጠበቅ የነበረውን የሰብሐዊ መብቶች መከበር ፤ ራስን በራስ የማስተዳደር ሙሉ መብት እና ሌሎች መሠረታዊ  የልማት እንቅስቃሴዎች በተነደፈው ህግ መንግስት መሰረት ለሕዝብ መሰጠት ሲገባቸው በተገላቢጦሽ ከርቀት በሪሞት  ኮንትሮል ከላይ ወደ ታች  በሚሰጡ ትህዛዞች መተግበር ጀመሩ::*

በዚህ የተነሳ የጋምቤላ ሕዝብ ለዓመታት ሲወደቅለት የነበረውን ለውጥ ባለማግኘቱ ጉልቻ ቢለዋወጡ ወጥ አያጣፍጥም  የሚባለው  አባባል በማጤን ያለፉትን የገዥ መደቦችና አሁን ያለሁን የኢህዴግ አባገነን መንግስት  በወረቀት  ላይ ያሰፈረውን መልካም ፖሊስ በወረቀት ላይ እንደ  አሰፋፈሩት ቀረ እንጂ ሲተገብሩት  አልታየም ለዚህም ነው  የአሁኑ መንግስት  ከአለፉት ገዥ መደባት የተለየ ተግባር ሲፈፃም ካልመታየቱ አልፎ ለክልል መንግሰታት  ተሰጠ የሚባልው መብትና የኢትዮጵያ ህገ-መንግስት ምዕራብያውያን ና ዛብታም ሀገራት ጋር መለመኛና ሕዝብን ማታለያ ከመሆኑም በቀር ለጭቁኑ የክልሉ ሕዝብ የፈየደው አነዳችም ነገር የለም::

## የጋምቤላ ክልል ሕዝብ ከኢህዴግ መንግስት ምን ይጠብቃል?

እንደ አጀማመሩ የደርግ መንግስት ለመጣል በተደርገው እንቅስቃሴ በሰላም ወዳድነቱ አርቆ አስተዋይነት የታወቀው የጋምቤላ ሕዝብ በራሱ ጉዳይ ላይ የመወሰን መብቱን ለማጎናፀፍ ላደረገው የትጥቅ ትግል ከደርግ ውድቀት በኃላ በኢትዮጵያ ህገ-መንግስት ሊረጋገጥለት ችለዋል።ሆኖም ግን በህገ-ምንግስቱ የተሰጠትን መብቶች ለመጠቀም በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴ የኢህዴግ መንግስት ባለ ሥልጣናት ሲያፋኑትና ሲአንገላቱት ይገኛል ። የክልሉ መንግሰት ለሕዝቡ የሚገባው መሰረታዊ ልማት በቅርበት የሚያወቀው በክልሉ ውሰጥ የሚገኙት የክልሉ ተወላጅ ከመሆናቸው አልፎ ለክትትልም የሚያመቹት እነሱ መሆን ሲገባቸው የኢህዴግ ካደሬዎች ሳይጣሯቸው አቤት የሚሉ፣ የማያውቁት እኔ ነኝ የማውቅልህ እያሉ ፣ ያልሰሙትን ሰምተናል እያሉ ሕዝቡን በምላሳቸው እየሸነገሉ የልማት ተጠቃሚ እንዳይሆን ሲያግዱት ቆይተዋል።

ኢህዴግም ከአለፉት ገዥ መደቦች ልምድ በመነሳት ሕዝቡን ለማዳከም ያሉትን ብሔር ብሔረሰቦች እርስ በርስ በማጋጭትና እንደኛው በአንደኛው ላይ በማነሳሳት ሕዝቡ ሲያናቆርና ሲያባላ ይገኛል። በዚህም የተነሳ የክልሉ ሕዝብ የልማት ተጠቃሚ ከመሆን ይልቅ የሩቅ ተመልካች ሆኖ ይገኛል።

የጋምቤላ ሕዝብ ከኢህዴግ መንግስት በጉጉት ሲጠብቀው የነበረውን ዕድገትና ለውጥ በእነዚህ ሰንካላና የግል ጥቅም አሳዳጅ በሆኑት ባለሥልጣናት ሰበብ ህብረተሰቡ የለውጡ ፍሬ ተጠቃሚ ሊያደርጋቸው አልቻለም ።

ሰላማዊ ሕዝብን ማፈናቀል ነፍስ ማጥፋትና ሴቶችን መድፋር እንደ ጀግንነት የተቆጠረለት የኢሕዴግ ሰራዊት እንደ የማንኛውም የሀገር መከላከያ ሰራዊት የሀገሩን ድንበር መጠበቅ ፣ ሕዝብን ከጠላት ሀገርን ከወረራ ለመጠበቅ የተቋቋመ አለኝታዎች ከመሆን ይልቅ በተቃራኒው ሕዝብን ሲበድሉ ይገኛሉ።ዳሩ ግን እጅግ አሰነዋሪው የኢህዴግ አባገነን መንግስት የአቋቋማቸው የመከላከያ ሰራዊት የተሰጣቸውን ሀገር የመጠበቅ ኃላፊነት ወደጎን በመተው አስነዋሪ ተግባራት ሰፈፅሙ ተስተውለዋል።

የኢህዴግ መንግስት ሀገሪቱ ከተቆጣጠረበት ቀን ጀምሮ በጋምቤላ ሕዝብ ላይ የፈፀማቸው አስነዋሪ ድርጊቶች ስፍር ቁጥር የለውም። ሰላማዊና አምራች የሆነው የወጣቱ ክፍል በዕየለቱ የተለየዩ ስሞች እየወጣ ማለትም ሌቦች፣ሽፍቶች፣አደገኛ ቦዘኔ፣እያለ በእነዚህ ስሞች በመጠቀም ወጣቱን ክፍል ብቻ በጠራራ ፀሐይ በጥይት ሲደበደብ ፣ሲያሳድድና ሲያስር ይገኛል። ይህ አልበቃ ብሎት በኢታንግና በጋምቤላ ከተማ በ1984 ዓ.ም (በ1992) በሰላማዊ የኑዌር ሕዝብ ላይ የደረገው የጅምላ ጭፍጨፋ፣ በዲማ ወረዳ ላይ የዕለት ጉርሻቸው ለማግኘት በወርቅ ቁፋሮ ስራ ላይተሰማርተው በነበሩት ጭቁን ስራ አጥ ወጣቶች ላይ የተደረገው የግድያ ዘመቻ ፣ በአኮቦ ወረዳ በኑወር አርሶ አደሮች ላይ የኢህዴግ ሰራዊት ያደረገው ግድያ እንዲሁም በጎደሬና(መዥንግር ዞን) አካባቢው ጭቁን መዥንገር ሕዝብ ላይ ሙሉ ኃይሉን በመጠቀም በምድር በእግረኛ በአየር በተዋጊ ኢሊኮፕተር በመታገዝ ሕፃን ወጣት፣ሽማግሌ አሮጊት ሳይል በተከታታይ ለሁለት ቀናት ዘግናኝ ጭፍጨፋ አካሄዷል ።

ሌላኛውና ትልቁ የመንግስቱን አረማኔነት የሚገለፅ ድረጊት በታህሳስ 3/1996 (2003) በጋምቤላ ሕዝብ ላይ ያደረገው ድርጊት ቃላት ሊገልፁትና ሊታመን በማይችል መንገድ የፈፀመው ድርጊት ነው።ከዚህም በመቀጠል አኝዋኮች ብቻ በሚኖሩበት ወረዳዎች በዲማ ወረዳ በአራተኛው ቀን ሕዝብን የመግደልና ንብረት የማቃጠል ዘመቻ በአቦቦና በፍኝዶ ወረዳዎችና አካባቢዎች በከባድ መሳሪያ የታገዘ ቤት የማቃጠልና ግድያ እንዲሁም ለአቅም ሒዋን ያልደረሱ ሴቶችን በመድፈር ሶስትና አራት ሆኖ በመፈራረቅ የፈፀሟቸው አፀያፊ ተግባራት እናትና ልጅ አንድ ላይ አድርጎ ርቃነ ስጋቸውን ሆኖ

በመፈራረቅ የፈፀሟቸው የመድፈር ተግባራት ከሰራዊቱ የማይጠበቁ አሳዛኝ እና ዘግናኝ ድርጊቶች ናቸው::

ይህ በዚህ ብቻ ሳያበቃ ከታህሳስ 3. 1996 የተጀምረው የግድያ ዘመቻ በሁሉም ወረዳዎች በማዳረስ ዘመቻውን ቀጥሎ እስከ 1998 ማብቂያ ድረስ ከፍተኛ በደል እና ኪሳራ አድርሰዋል :: በነዚህ የሰቃይና ዋይታ ዓመታት ሕይወታቸው ያጡት የአኝዋ ሕዝብ አሁን ከሚባለው ቁጥር በላይ እነደሆነና በጋምቤላ ከተማ ብቻ የወደመውም ንብረት 1.5 ሚሊዮን ገንዘብ እንደሚገመት ይገለፃል::
በዚህ የኢህዴግ ሰራዊት ዘመቻ ወቅት በክልሉ አገልግሎት ሰጪ የነበሩት ተቋማት በተለይ የአኝዋክ ወረደዎች እንደ ት/ቤቶች የጤና ተቋማት የመሳሰሉት ውስጥ የነበሩ አገልግሎት መስጫ ንብረቶች በሙሉ በማውደምና በማቃጠል ቤቶችን እንደ ጦር ካምፕ ሲጠቀሙበት ተስተውለዋል :: በየሰፈሩበት ወረዳና ቀበሌ ያሉት የገበሬ ሚስቶች ውሃ በማስቀዳት ፤እንጭት በማስፈለጥ ፤ምግብ በማብሰል አልፎ እንደ ሴትኛ አዳሪ አድረገው ሲለዋወጡባቸው ታይተዋል :: ገበሬዎቹም ሚስቶቻቸው ለመጠየቅ በሚሄዱበት ጊዜ ድብደባና አፀያፊ ድርጊቶች ባሉበት በሚስቶቻቸው ላይ ሰፈፀምና አንዳንድ ባሎች ለጥየቃ ስለሄዱ ብቻ ሕይወታቸው በወታደሮች እጅ አልፏል ::

ይህ አልበቃ ብሎ የኢህዴግ መንግስት በሰራዊቱ የተፈፀመውን ድርጊት ከአለም አቀፍ መንግስታት ለመደበቅ ከፍተኛ ሙከራ አድርጓል:: የደረገውን ሙከራ ግን ተጎጂ የሆነው የጋምቤላ ሕዝብ ልጆች ባደረጉት መረባረብ ሴራው ሊጋለጥ ችሏል::

አሁንም የተጋለጠው ገመናቸውን ጋህድ እንዳይወጣ ለመከላከል ባደረጉት ሙከራ ተጎጂ የሆነውተማረው የአኝዋ ክፍል ጠንሳሽ አድርገው በመቁጠር ከአለም አቀፉ ህብረተሰብ ዕይታ ውጪ ለማድረግ በማሰብ በተለያዩ የኢትዮጵያ እስር ቤቶች እየተሰቃዩ ይገኛሉ::

ዳሩ ግነ ጭፍጭፋውና ገደዮቹ የሠራዊቱ አባላት እንዲሁም በወንጀሉ የተሳተፉት ግለሰቦች በወንጀሉ ሳይጠየቁ የፈፀሙት ድርጊት እንደ ጀግንነት ተቆጥሮላቸው የማረግ እድገት እስከማግኘት ድረስ የደረሱና የቀሩት ግለሰቦች ደግሞ በተጎጂው ህብረተሰብ ላይ በዛቻና በምን አለብኝነት ህብረተሰቡን በማሰቃየት ላይ ይገኛሉ::

## ጋህነን (GPLM/F) በጋምቤላ ሕዝብ ችግር ላይ ያለው አቋም

ጋህነን/ግ የጋምቤላ ሕዝብ ችግሮች ሊፈቱ የሚችሉ በአለፉት አሻንጉሊት ገዥዎች እና የኢህዴግ መንግስት በሚወጡት ፖሊሲና ደንቦች አለመሆኑን ያምናል::
የጋምቤላ ሕዝብ ነፃነቱንና ስብህናውን ከምንም በላይ የሚመለከተው ሕዝብ ነው::
በዚህም የተነሳ በጨቋኝ ገዥ መደቦች እየተዘረጋበት ያለው የጭቆናና የአፋና መረብ የሥልጠን ቅብብሎሽ ለማስቀረትና ነፃነቱን ለማጎናፀፍ የሚደረገውን ትግል በትክክል የታለመለትን ግብ እንዲመታ ጋህነን/ግ ሕዝብን የማንቃት ስራ ቅድሚያ በመስጠት ይንቀሳቀሳል:: የሕዝቡንም ንቃት ህሊና አሁን ካለው ደረጃ ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ አብይ ተግባሩ ነው::
ጋህነን/ግ የሕዝቡን ሮሮ፤ሥቃይ፤ፍላጎትና ጥያቄ መሠረት በማድረግ የሚከተሉት ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ ቆርጦ ተነስቷል::

፩. አለማቀፋዊ ደንቦች ህግጋት በማይቃረን መልኩ በማንኛውም የትግል አቅጣጫ በመጠቀም ለሕዝቡ ነፃነት ሲል ይቆማል የሕዝቡንም ፖለቲካዊ፤ኢኮኖሚዊ፤ ማህበራዊ ጥቅሞች በጋራ ተደጋፊነት የራስን ዕድል በራሰ የመወሰን መብት እንዲረጋገጥለት ጋህነን/ግ በፅኑ ይታገላል::

፪. እውነተኛ የክልሉ ሰላምና አንድነቱ ሊመጣ የሚችለው ሕዝቡ በራሱ ጉዳዮች ላይ የመወሰን መብቱ በህገ-መንግስቱ እንደተደነገገው በተግባር ሲተረጎም መሆኑን ጋህነን/ግ በፅናት ያምናል።
ስለዚህ ዜጎች የሥልጣን ባለቤትነታቸውን በተግባር በማረጋገጥ የሕዝቡን ንቃተ ህሊና ከማሳደግ ጎን ለጎን የዓለም ሰላምን ለዲሞክራሳዊ መብቶችን በማረጋገጥ ረገድ ጋህነን/ግ አሰፈላገውን አስተዋፆ ያበረክታል።

፫. በጋህነን/ግ እይታ ልማት ማለት ለክልሉን ሕዝብ መሰረታዊ የሆኑት የልማት ተቋማትና አገልግሎት ሰጪ ባለሙያዎች ማደራጀትና ማሰልጠን ማለት ነው። ያልተገናኙ ወረዳዎችን በመንገድ በማገናኘትና ገበሬውን ምርቱን ገበያ ላይ እንዲውል በማበረታታትና ሀገር አቀፍ ገበያ  ላይ ተወዳዳሪ እንዲሆን ማድረግ፤ሕዝቡን የንፁህ ውሃ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ፤በአቅራቢያው የጤና ተቀዋም  የትምህርት ተቋማት በመገንባትና አገልግሎት በሚገባው እንዲያገኝ ማድረግ እደሆነ ጋህነን/ግ ያምንበታል።በኢሕዴግ ዘንድ ግን ል ማት ማለት ካድሬዎችን ማሰልጠን ፤ለሹማምንቶች የሚደረግ የደሞዝ ጭማሪ ፤በተራበው ህብረተሰብ ስም የሚጠየቅን ዕርዳታ ለተገቢው ሕዝብ መስጠት ሲገባው ለካድሬዎቻቸው ና ለአባላት መመልመያ ማዋል ፤ በግብር መልክ ከድሃው ህብረተሰብ የሚሰበሰበውን ገንዘብ ለጦር መሳሪያ ግዢ በማዋልና መልሶ የገዛ ሕዝቡን መፍጅት ማለት ነው።

፬. ጋህነን/ግ የክልሉ ደን ፤እንሰሳትና ዓሳ ሀብቱን እንዲሁም ለም መሬቱን በመጠበቅና ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ አሰፈላጊውን የመከላከያ ስልት ይቀሳል፡ የክልሉን ሕዝብ እንደ አቅሙ የበኩሉን አሰተዋፆ እንደያበረክት ያበረታታል።

፭. ሥራ አጡን የህብረተሰብን ክፍል ፡ደጋፊ ባለማግኘት ትምህርታቸውን ያቋረጡ ፡ወላጅ አልባ ሕፃናት ፤ አዛውንቶች ፤ሴቶችና አካለ ስንኩላን የሆኑ ዜጎችን መልሶ ተስፋ እንዲዘሩና ራሳቸውን እንዲችሉ ድርጅታዊ ኃላፊነቱን ይወጣል።

፮. በህግ የበላይነት በመከባበርና በመደጋገፍ የሕዝቦች የጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ከሚፈጥሩ ዲሞክራሳዊ መንግሰታትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ድርጅታችን የጠበቀ ግንኙነት ያደርጋል።

## ማጠቃለያ

አሁን ያለውን የከፋፍለህ ግዛ የኢህዴግ አምባገነን መንግስት ሥርዓት  ሕዝብን ከሕዝብ ማጋጭት ፤ በማይጨበጥ ልማት ስም ሕዝቡን በማታለለል ፤ በጭፍን የሐሴት ፕሮፖጋዳ ህብረተሰበን ማዋከብ ይህን የማን አለብኝነት ትግባሩ ለሕዝብ በማጋለጥና ሕዝቡ የስልጣን ባለቤት ማድረግ።
የክልሉ ሕዝብ ሥልጣን  ባለቤትነትና የህገ-መንግስት የበላይነት ላይ የተመሰረተ አመራር እስኪሰፈፍን ድረስ ጋህነን/ግ ከአለም አቀፍ ህብረተሰብ እና ዲሞክራሲ አራማጅ መንግስታት ጋር እጅ ለእጅ በመሆን አሰፈላጊውን ሁሉ ትግል ያደርጋል።

---

E-Mail: gplma_1977@yahoo.com
Tel No- + 88216212216009